# ማንን ጠላህ፣በሉኝ?

ማንን ጠላህ ፣ በሉኝ ፣ ሰው መሳይ ፣ በሸንጎ
ጭምብል ያጠለቀ ፣ የኦነግ ማደጎ
ሸፍጥና ተንኮሉን ፣ በልቡ ሸሽጎ
ባንድነት ከለላ ፣ ከህዝብ ፣ መሃል ሰርጎ
መዋሸትን ሙያ ፣ መመሪያው አድርጎ
ሲሰብክ የሚያመሽን ፣ ሁሉን ፣ እንደ በጎ ።

ማንን ጠላህ ፣ በሉኝ ፣ እስስት ተለዋዋጭ
ወሬ እያሳመረ ፣ በደረቅ የሚላጭ
አይኑን ፣ በጨው ታጥቦ ፣ የሚዋሽ በግላጭ
ለራሱ የማይበጅ ፣ የባዕድ አሽቃባጭ
ከቤት ለቅሶ እያለ ፣ ጎረቤት አዳማጭ
ሲያምኑት የሚከዳ ፣ የሰው አንጀት ፣ ቆራጭ ።

ማንን ጠላህ ፣ በሉኝ ፣ መንታ ምላስ ፣ ያለው
ማታለል ማጭበርበር ፣ ሞያ የመሰለው
የለበጣ ፍቅርን ፣ ሰማይ የሚሰቅለው
ከጎጡ ሳይወጣ ፣ የሚንከባለለው
ካፍንጫው የሚርቅ ፣ እይታ የሌለው
ገና ሳይገነባ ፣ ሊያፈርስ የቸኮለው
እንደተወደደ ፣ መኖር ያላደለው ።

እኮ ማንን ፣ ጠላሁ ፣ እጅጉን አምርሬ
ሊያሾፍ የሚከጅል ፣ በወገን ባገሬ
ተግባር የጎደለው ፣ አሳማሪ ወሬ
የሆነ ያልሆነ ፣ ዲስኩር ቀባጥሬ
በተስፋ በምኞት ፣ ሁሉንም አስሬ
እኖራለሁ የሚል ፣ ባገር ተከብሬ
የተወናበደ ፣ ብስል መስሎ ጥሬ ።

ማንን ጠላህ ፣ በሉኝ ፣ ስሜት የሚያስነሳ
ሱሴ ፣ ሱሴ ፣ እያለ ፣ እንደ እባብ ፣ ለስላሳ
የመጣበት ስፍራ ፣ መስሎት የተረሳ
በመንደር የሚያስብ ፣ ዘንድሮም ጨንባሳ
ከተቀመጠበት ፣ ለፍታም ያልተነሳ
ዘውጌ ጨለምተኛ ፣ የሃገር ነቀርሳ ።

ማንን ጠላህ ፣ በሉኝ ፣ የጎጠኞች ሙሴ
ሰውር መልዕክተኛ ፣ ያፍራሽ እንደራሴ
የተገንጣይ ፣ ቀኝ እጅ ፣ የኢንሳ መነኩሴ
የአረብ ተላላኪ ፣ የባዕድ አንካሴ
ያንገፈግፈኛል ፣ ሳስበው ለራሴ
ተፀይፋዋለች ፣ ጠልታዋለች ነፍሴ ።

ማንን ጠላህ ፣ በሉኝ ፣ አብይና ለማን
በኢትዮጵያ አንድነት ፣ አሿፊ ድኩማን
ሲከፈቱ ተልባ ፣ አቀንቃኝ ጨለማን
እንኳን የያዝነውን ፣ ህልምን የሚቀማን
ፅንፈኛ ዘረኛ ፣ ትንሽ ፣ የሰው ኩርማን
ባገር ላይ ፣ የመጡ ፣ የዘመኑ እርግማን
ያመናቸውን ልብ ፣ አቁስሎ ያደማን ።

ታዛቢው

March 18, 2019